የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ የድጋፍ ድርጅት በዩናይትድ ኪንግደም
Coalition for Unity and Democracy Party Support Organisation in UK
(CUDP-SOUK)

# ዛሬም የሰማዕታት ደም ይጣራል!!!

የኢትዮጵያ ህዝብ በታሪኩ ለመጀመሪያ ጊዜ መሪዎቹን የመረጠበት የዴሞክራሲ ቀን ግንቦት ሰባት ቀን ተዘክሮ ውሎአል። ወያኔ አምኖበት ሳይሆን አስቀያሚ ፖለቲካውን ለመሸፋፈንና ተቀባይነትን ለማግኘት ባካሄደው ምርጫ ድባቅ የተመታበትን ብቻ ሳይሆን፤ ድምጼን አላሰርቅም ብሎ ህገ-መንግስታዊ መብቱን ተጠቅሞ ሰላማዊ ተቃውሞ ያሰማውን ሕዝብ ባደለበው የአጋዚ ጦር በግፍ ያስጨፈጨፈበት የመስዋዕትነትና የሰማዕትነት አንደኛ ዓመት መታሰቢያ ደግሞ ሰኔ አንድ ቀን 1998 ታስቦ ውሏል። ይህ እለት አረመኔው ወያኔ ቁጥራቸው ከ40 በላይ የሆነ ወጣቶች፤ ጎልማሶችና አዛውንት ወገኖቻችንን ደም በግፍ ያፈሰሰበት እለት በመሆኑ በጥልቅ የሀዘን ስሜት የምናስታውሰው ብሎም የሰማዕታቱን የትግል አርማ አንስተን ትግሉን ለማፋፋም ቃል የምንገባበት ልዩ እለት ነው።

አንድ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የተለያዩ አመለካከቶችና አማራጮች መኖርና ሕዝብ የራሱን መሪዎች የሚመርጥበት፤ ሰብአዊ መብት የሚከበርበትና የህግ የበላይት የተረጋገጠት፤ ዜጎች ያለ ፍርሃት በነፃነትና በእኩልነት የሚኖሩበት ሥርዓት ነው። ዛሬ በኢትዮጵያ አለ የሚባለው አፍአዊ ዴሞክራሲና አምባ-ገነናዊ ዘረኛ አገዛዝ ነው። ፈላጭ ቆራጩና ዘረኛው ወያኔ ዴሞክራሲ አመጣሁ የሚለው መስሎ በመቅረብ የልመና ኮሮጆውን ለመሙላት እንጂ፤ እውነተኛ ባህሪው የግንቦት 1997 ምርጫን ተከትሎ በተፈጸመው የድምጽ ማጭበርበር የህዝብ ጭፍጨፋ ፋሺስታዊ ድርጊት በገሃድ ታይቶአል። ወያኔ ለአስራ አምስት ዓመታት እንደለፈፈው በሀገራችን ሰላምና መረጋጋት፤ ልማትና ብልጥግና፤መልካም አስተዳደር፤ የሰብአዊ መብት ከበሬታና ነፃነት የሚባል ነገር አላመጣም። የአስራ አምስት ዓመታት የወያኔ አገዛዝ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያስገኘው ነገር ቢኖር ጥቂቶች በላቡ ጠብታ ሲንደላቀቁ እሱ የበይ ተመልካች ሆኖ በረሃብ አለንጋ መጠበስ፤ በነጭ ለባሽ፤ በኮርና በካድሬ ቁም ስቃዩን እያዩ መብቱን ተገፎ በባርነት መኖር ሆኖአል።

ወያኔ ከውጭ ጌቶቹ በሚሰጠው የኢኮኖሚ ድጎማ፣ ቴክኒካዊና ዲፕሎማስያዊ ድጋፍና ባነገበው ጠመንጃ ተማምኖ የአፈናና የብዝበዛ መዋቅሩን አጠናክሮ የሕዝባችን ሰብኣዊና ዴሞክራሲያዊ መብት በመርገጥ ላይ ይገኛል። ሕዝብ ወያኔን ባለመምረጡ የበቀል እርምጃ ሰለባ ሆኗል። ስቃይና መከራውን ያሳየዋል። ዛሬም በየቦታው ዜጎች የተለየ የፓለቲካ አመለካከት በመያዛቸው ብቻ ይዋከባሉ። ለግፍ እስራትና ግድያ ይዳረጋሉ። ከሥራና የመኖሪያ ቦታቸው ይፈናቀላሉ። በጎሳ፤ በሃይማኖትና በጎጥ ይከፋፈላሉ። የመናገር፣ የመሰብሰብ የመጻፍና የሀሳብን በነፃ የመግለጽ ዴሞክራስያዊና ተፈጥሮአዊ መብቶች ታግደዋል። በጥቅሉ ወያኔ አገሪቱ ወደ መካከለኛው የጨለማ ዘመን እየጎተታት ነው። በራሳቸው ጥቅም የታወሩ የውጭ ሃይሎችም የሚጫወቱት የፖለቲካ ቁማርም በህዝባችን ላይ የሚደርሰውን መከራ አባብሶታል።

በተለይም የቅንጅት አባላትና ደጋፊዎች የወያኔ ግፍ ግንባር ቀደም ገፈት ቀማሾች ሆነዋል። በህዝብ ዘንድ ተወዳጅ የሆነውን ለማጥፋት ወያኔና አጫፋሪዎቹ በሚወስዱት ግብታዊ እርምጃ በሀገሪቱ ውስጥ አለመረጋጋት እንዲፈጠር እያደረገ ነው። የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆችና የህዝብ ተመራጮች የሆኑት

መገናኛ ስልክ 07946644831 የፖ.ሳ.ቁጥር 57105 London SW6 2QJ ኢ.ሜል kinijit97@yahoo.co.uk
Contact tel 07946644831 PO Box 57105 London SW6 2QJ E-mail kinijit97@yahoo.co.uk

የቅንጅት መሪዎች ዛሬም በግፍ ታስረው በፍርድ ስም በአደባባይ ድራማ እየተሰራ በመጉላላት ላይ ናቸው። የነፃው ፕሬስ ባለሙያዎችና የሙያ ማህበራት መሪዎች አባላት በእስር ይማቀቃሉ። በአንጻሩም በጦር ወንጀለኝነት የሚፈለጉ ነፍሰ-ገዳዮች ለፍርድ ሊቀርቡ ቀርቶ በሰኔና በህዳር የተካሄደው የጅምላ ጭፍጨፋ እንዲጣራ የቀረበው ሕዝባዊ ጥያቄ ዛሬም መልስ አላገኘም።

የግፍ ፅዋው ሞልቶ መፍሰስ ትግሉን የበለጠ የሚያቀጣጥል እንጂ የሚያበርደው ሊሆን ከቶ አይችልም። ቅንጅት ያነሳቸው መሰረታዊ ዴሞክራሲና የሰብአዊ መብት መርሆች በተግባር እስከሚረጋገጡና የኢትዮጵያ ህዝብ የፍትህ፣ የእኩልነትና የነፃነት ጥያቄ መልስ እስከሚያገኝ ድረስ ትግሉ የሚቆም አይደለም። በግፍ የፈሰሰው የሰማዕታት ደም ነፃነትን ሳይዋጅ መና ሆኖ የሚቀር አይሆንም። የወያኔን ከፋፋይና ዘረኛ ፖሊሲ ለማስወገድና የዜጎች ሁሉ መብት የተከበረባት ኢትዮጵያ እውን እስክትሆን ድረስ የተቀነባበረና ሁሉን አቀፍ የሆነ የጋራ ትግል ማካሄድ ወቅቱ የሚጠይቀው ጉዳይ ነው። ከዛሬ ላይ ቆመን ነገን ስናስብ ለሚታየን የተስፋ ብርሃን ቁልፉ በአንድነት ቆሞ ትግሉን ማጠናከር ብቻ ነው።

ስለ ትግል በምንነጋገርበት ወቅት ብቃት ያለው አመራር መኖር ጉዳይ ቻል የሚባል አይደለም። ለመብቱ ለመታገል ቆርጦ የተነሳህን ህዝብ አቅጣጫ ማስያዝና ተገቢውን አመራር መስጠት የሚችል ድርጅታዊ ብቃት ማጎልበት በዋዛ ሊታይ አይገባም። አመራር የሌለው ህዝብ እረኛ የሌለው መንጋ ይመስላል። ስለሆነም ተቃዋሚ ድርጅቶች በተለይም የህዝብን አመኔታ ያገኘው ቅንጅት ያለበትን ታሪካዊና ህዝባዊ አደራ ተገንዝቦ የተፈጠረውን ክፍተት በአፋጣኝ ሞልቶ መንቀሳቀስ ይጠበቅበታል። ከግላዊ ስሜት ተላቀን፣ ሕዝባዊ አርማችንን አንግበን ወቅቱ የሚጠይቀውን መስዋዕትነት የመክፈል ትውልዳዊ አደራ አለብን። ትግል እስከ ድል እያለ የሰማዕታት ወገኖቻችን ደም ዛሬም ይጣራልና። ለጥሪው መልስ መስጠት የሁላችንም ግዴታ ነው።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ
ሰኔ 1 ቀን 1998
ለንደን